አህዛዊ መረጃ

ICRC

## ኢትዮጵያ

# አሀዛዊ መረጃ

## እአአ ከጥር እስከ ሰኔ 2020 ዓ.ም




በጎሳ ግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች አካላዊ ርቀተቻውን በመጠበቅ የዓአቀመኮና ኢቀመማ በጋራ ያከፋፈሉትን የዘር እህል እርዳታ በተቀበሉበት ወቅት በኮሮና ቫይረስ መከላከል ላይ ያተኮረ ትምህርት ሲሰጣቸው፤ያሶ ወረዳ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል (እአአ 2020 ዓ.ም)።

የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ (ዓአቀመኮ) ስራውን በኢትዮጵያ የጀመረው እአአ በ1977 ዓ.ም በኢትዮጵያና ሱማሌ መካከል ከተካሄደው የትጥቅ ግጭት አንስቶ ነው። የዓአቀመኮ በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት እስረኞች ዓለም አቀፋዊ ደንቦችንና መስፈርቶችን መሠረት ባደረገ መልኩ ሰብዓዊ ክብራቸው ተጠብቆና ተከብሮ መያዛቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል ማረሚያ ቤቶችን መጎብኘትና የአካል ጉዳተኞች ማቋቋሚያ ፕሮግራም የአካል ጉዳተኞች የመልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎትን በጥራትና በዘላቂነት ለማግኘት እንዲችሉ መርዳት ናቸው። ከኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር (ኢቀመማ) ጋር በመተባበር በትጥቅ ግጭትና በሌሎች ብጥብጦች ምክንያት የተነጣጠሉ ቤተሰቦችን እንደገና ግንኙነት እንዲመሰርቱ ጥረት ማድረግና በግጭትና በብጥብጥ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች እርዳታ የመስጠት ተግባርም ያከናውናል። ከዚህ በተጨማሪም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ እውቀትን ለመከላከያና ፖሊስ ሀይል አባላት፣ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ለህግ ባለሙያዎችና ለፖሊሲ አውጪዎች ያሰራጫል። እአአ ከመጋቢት ወር 2020 ዓ.ም ጀምሮ የዓአቀመኮ በአገሪቱ የኮሮና ቫይረስ ክስተት ከፈጠረው ሁኔታ ጋር ተግባራቱን በፍጥነት በማጣጣምና በማቀናጀት ቫይረሱ ላስከተለው ቀውስ ምላሽ የመስጠት ተግባራቱን እያፋጠነ ይገኛል።

## ማረሚያ ቤቶች

እአአ ከጥር እስከ ሰኔ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ፤

- በአገሪቱ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ባሉ **19** ማረሚያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙና ቁጥራቸው ከ**17,180** የሚበልጡ ታራሚዎችን ከመጎብኘቱም በላይ **30** ታራሚዎችን በግለሰብ ደረጃ ተከታትሏል። ለእነዚሁ ማረሚያ ቤቶች የንጽህና መገልገያዎች፣ አልባሳት፣ብርድልብሶችና የመዝናኛ መገልገያዎችን ጨምሮ ሌሎች እርዳታዎችን በመስጠት ከ**8,200** የሚበልጡ ታራሚዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- በተለያዩ የፌዴራልና ክልል ማረሚያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ **439** ለጉዳት የተጋለጡ የአካል ጉዳተኛ ታራሚዎች ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዲችሉ የህክምና ነክና ህክምና ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን (የግል ንጽህናና የመንቀሳቀሻ መርጃ መሳሪያዎች) ለግሷል።
- በ**9** ማረሚያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የውሀና የቆሻሻ ማስወገጃ መስመሮችን በመገንባትና በመጠገን **2,900** ታራሚዎችን የተሻሻለ የውሀና የጽዳት አገልግሎት ተጠቃሚ አድርጓል።




የዓአቀመኮ ለጎንደር ማረሚያ ቤት ማረሚያ ቤቱ የኮሮና ቫይረስን ለመከላከል ለሚያደርገው እንቅስቃሴ በእርዳታ የሰጠው የንጽህና መገልገያ ቁሳቁሶች፤ ጎንደር ከተማ፤ አማራ ክልል (እአአ 2020 ዓ.ም)።

- ከ**50,000** በላይ ታራሚዎችን ለያዙ **41** ማረሚያ ቤቶች ከ**290,000** የሚበልጡ ሳሙናዎች፣ **170** ቋሚ የእጅ መታጠቢያዎች፣ **162** ሊትር ክሎሪን፣ **98** ዲስፔንሰሮች፣ **330** ሊትር የእጅ ብክለት ማጽጃ ኬሚካል፣ **1,000** የኮቪድ-19 መከላከያ መረጃ መልዕክቶችን የያዙ ፖስተሮችና የብክለት መከላከያ ኬሚካሎች እርዳታ አድርጓል።
- ለ**4,576** ታራሚዎች የነጻ ስልክና የአየር አገልግሎት አቅርቦት በማድረግ ታራሚዎቹ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በቋሚነት ለማስቀጠል አስችሏል።

## የተነጣጠሉ ቤተሰቦች

እአአ ከጥር እስከ ሰኔ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውሰጥ የዓአቀመኮ፤

- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባለው የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የተቋቋመ የለይቶ ማቆያ ማዕከልን ጨምሮ በሰባት የለይቶ ማቆያ ማዕከሎች ውስጥ ለተቀመጡና ከስደት ለተመለሱ 7,446 ኢትዮጵያውያን የመሰረታዊ ቁሳቁሶች እርዳታ አድርጓል። 340 አጋር የለሽ ታዳጊ ልጆችን ጨምሮ 2,533 ከስደት ተመላሾች ከሚወዷቸው ሰዎች ጋር ግንኙነት ለማድረግ እንዲችሉ የስልክ ጥሪ አገልግሎት አቅርቦት አድርጓል።
- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር ስደተኞችና ተመላሾች በየአገሮቻቸው ከሚገኙ ቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማስቀጠል የሚያስችሉ 48,155 ነጻ የስልክ ጥሪዎች እንዲያደርጉ አስችሏል።
- በኢትዮጵያና ውጪ አገራት የጠፉባቸው ዘመዶቻቸውን በመፈለግ ላይ ካሉ ሰዎች 268 የአፋልጉኝ ጥያቄዎችን የተቀበለ ሲሆን ከአነዚህም መካከል የ34 ሰዎችን አድራሻ አግኝቷል።
- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር በግጭትና በብጥብጥ ምክንያት በተጠፋፉ የቤተሰብ አባላት መካከል 468 የቀይ መስቀል መልዕክቶች ልውውጥ እንዲካሄድ አድርጓል።
- የተነጠሏቸውን የቤተሰብ አባላት በመፈለግ ላይ ያሉ 396 የደቡብ ሱዳን ስደተኞችን ፎቶዎች የያዙ ሁለት አዲስ ጥራዞችን አሳትሟል።

## ጤና

እአአ ከጥር እስከ ሰኔ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውሰጥ የዓአቀመኮ፤

- በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ ስድስት የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ጣቢያዎችና አምስት ሆስፒታሎች በአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ለመስጠት እንዲችሉ መሰረታዊ የጤና መገልገያዎችንና የአስቸኳይ ጊዜ ቁሳቁሶችን የያዙ ሳጥኖችን ለግሷል።
- በሁሴና በጭናቅሰን እንዲሁም በቱሊጉሌድና መዩ ወረዳዎች ለሚገኙ አራት የጤና ማዕከሎች ወርሀዊ የቴክኒክ እገዛ፣የህክምና መገልገያዎች፣ የቅድመ ወሊድ ምግብ ነክ ያልሆነና የልጆች ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ እርዳታ በመስጠት በማዕከሎቹ ውስጥ ልጆቻቸውን የወለዱ 1,300 እናቶችን ተጠቃሚ አድርጓል። እንዲሁም የዓአቀመኮ የግል የበሽታ መከላከያ ቁሳቁስ (ሽርጦች፣ ቦት ጫማዎች፣የእጅ ጓንቶች፣ፈሳሽ ሳሙናዎችና ቋሚ የእጅ መታጠቢያዎች) እርዳታ ከላይ በተጠቀሱት ወረዳዎች ለሚገኙ የጤና ማዕከሎች ሰጥቷል።




አራስ እናት የዓአቀመኮ ድጋፍ በሚያደርግለት የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ማዕከል አዲስ የወለደችውን ልጅ ስትንከባከብ፤ጭናቅሰን ወረዳ፤ኦሮሚያ ክልል (እአአ 2020 ዓ.ም)።

- ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ተቋምና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኮቪድ-19 ምክንያት የሚሞቱ ሰዎችን አስከሬን በአግባቡ ለመያዝና ለማስተናገድ የሚረዱ አራት ስልጠናዎች ለ70 የጤና ባለሙያዎች ለማዘጋጀት የሚያስችል ድጋፍ አድርጓል።
- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር በአማራ፣በኦሮሚያ፣አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ ሱማሌና ሀረሪ ክልሎች ውስጥ ለተቋቋሙ 17 የኮቪድ-19 የህክምና ማዕከሎች 2,500 ፍራሾች፣ 2,500 አንሶላዎችና 20,000 ሳሙናዎችና የበሽታ ብክለት ማጽጃ ኬሚካሎች ሰጥቷል።

## በግጭት ጉዳት የደረሰባቸውና ያልደረሰባቸው ማህበረሰቦች

እአአ ከጥር እስከ ሰኔ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውሰጥ የዓአቀመኮ፤

- በምስራቅ ሐረርጌና ምስራቅ ወለጋ (ኦሮሚያ ክልል)፣ በፋፋንና ኤረር (ሱማሌ ክልል) በካማሺ (ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል) በማህበረሰባዊ ግጭት ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው 74,300 ቤተሰቦች መልሰው ኑሮአቸውን እንዲመሰረቱ 151 ቶን የበቆሎ፤ 36 ቶን የማሽላ፤ 50 ቶን የአተርና 56 ቶን የጤፍ ዘር እህል እርዳታ ሰጥቷል። የዓአቀመኮ ለእነዚሁ ሰዎች የዘርና የእርሻ ግብዓቶች ፍላጎታቸውን ለመሸፈን እንዲችሉ ከ1,000 እስከ 1,400 ብር የሚደርስ የገንዘብ እርዳታም አድርጓል።
- በቋራ (አማራ ክልል) እና ቱሊጉሌድ (ሱማሌ ክልል) በማህበረሰባዊ ግጭት ምክንያት ለተፈናቀሉ 2142 ሰዎች የፕላስቲክ መጠለያዎች፣ ምንጣፎች፣ ብርድልብሶች፣ ጀሪካኖች፣ ሳሙናዎችና የምግብ ማብሰያ ቁሰቁሶች እርዳታ አድርጓል።




የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ ፕሬዝዳንት (ዓአቀመኮ) ፒተር ሞረር በቅርቡ በኢትዮጵያ ጉብኝት ባደረጉበት ጊዜ በጎሳ ግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን ሲያዳምጡ፤ሳሪር ቀበሌ ቱሊጉሌድ ወረዳ፤ሱማሌ ክልል (እአአ 2020 ዓ.ም)። (የኮሮና ቫይረስ ከመከሰቱ በፊት)

- በሰሜን ጎንደር (አማራ ክልል) እና በጋምቤላ ክልል በጎሳ ግጭት ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው 3,270 ሰዎች የገንዘብ እርዳታ ሰጥቷል።
- በሱማሌና ኦሮሚያ ሰሜናዊ ድንበር አካባቢዎች ለሚኖሩ 450,000 ከፊል አርብቶ አደር ማህበረሰብ የቤት እንስሳዎችን የጸረ እንስሳት በሽታዎች መከላከያ ክትባት (ለአንትራክስ፣ብላክሌግ እና ፓስትሮላ) ለመስጠት የሚያስችል እርዳታ አድርጓል። በዚህም 196,800 ሰዎች ተጠቃሚ ሆነዋል።

## የውሀና መኖሪያ አካባቢ

እአአ ከጥር እስከ ሰኔ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ፤

- በሱማሌ ክልል በፋፋን ዞን በካሊያሌ ቀበሌ የከርሰምድር ውሀ ማጠራቀሚያ ኩሬ ግንባታን በማጠናቀቅ **4,500** ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሐረርጌ ዞን በጫሎና ሮጌ ቀበሌዎች ውስጥ የጤና ኬላና የእንሰሳት መድሀኒት ቤት በመገንባት **10,000** ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- በጭናቅሰን (ሱማሌ ክልል) እና በቱሊጉሌድ (ኦሮሚያ ክልል) ውስጥ የሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ተቋሚትን የውሀ አገልግሎት አውታርን አድሷል።
- በሮጌ ቀበሌ የመጀመሪያ ደረጃ የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራን አጠናቅቋል። ይህ ጉድጓድ በግጭት ጉዳት የደረሰባቸው **10,000** የማህበረሰቡ አባላትን ተጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል።




በጎሳ ግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች በዓአቀመኮ ከተገነባው የመጠጥ የዉሀ ጣቢያ ውሀ ሲቀዱ፤ አወጃብር ቀበሌ፣ባቢሌ ወረዳ፣ሱማሌ ክልል (እአአ 2020 ዓ.ም) (የኮሮና ቫይረስ ከመከሰቱ በፊት)። (የኮሮና ቫይረስ ከመከሰቱ በፊት)

## የአካል ጉዳተኞች

እአአ ከጥር እስከ ሰኔ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ፤

- በኦሮሚያ፣ አማራ፣ሀረሪ፣ ደቡብ አትዮጵያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ሱማሌ ክልሎች ውስጥ ለሚገኙ ዘጠኝ የአካል ጉዳተኛ ማቋቋሚያ አጋር ማዕከሎች ቋሚ የእጅ መታጠቢያዎች፣የንጽህና መገልገያ ቁሳቁስና የኮቪድ መከላከያ መረጃ መልዕክቶችን የያዙ ፖስተሮች አሰራጭቷል።
- ከአትዮጵያ ብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ማህበር ፌዴሬሽን ጋር በመተባበር ስለ በሽታው ያላቸውን ግንዛቤ ለማዳበርና የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የሚያሰችሉና በአራት ዋና ዋና ቋንቋዎች የተዘጋጁ መልዕክቶች በክልልና ብሔራዊ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች አማካኝነት ለአካል ጉዳተኞች እንዲሰራጩ አድርጓል።
- ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከላይ ከተጠቀሰው ፌዴሬሽን ጋር **12** የለይቶ ማቆያና የህክምና ማዕከላት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ መሆናቸውን እና በማእከሉ የሚሰሩ ሰራተኞች ስለ አካል ጉዳኞች ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ በተደረገ ጥናት ላይ ተሳትፏል።




በዓአቀመኮ ድጋፍ በባህር ዳር የአካል ጉዳተኛ ማዕክል አማካኝነት በኮቪድ-19 የህክምና ማዕከሎች ውስጥ ለሚሰሩ ነርሶችና ሀኪሞች በአገር ውስጥ የፊት መከላከያ ጭምብሎች ሲመረቱ፤ባህር ዳር፤ አማራ ክልል (እአአ 2020 ዓ.ም)።

- ስድስት የአካል ጉዳተኛ ማቋቋሚያ ማዕከሎች በሆስፒታልና ማግለያ ማዕከሎች የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች የሚጠቀሙበት **4,000** ጭምብሎችን (face masks) በአገር ውስጥ ለማምረት የሚያስችል ድጋፍ አድርጓል።
- **2,918** የአካል ጉዳተኞች የዓአቀመኮ እርዳታ በሚያደርግላቸው ዘጠኝ የአካል ጉዳተኛ ማቋቋሚያ ማዕከሎች ውስጥ አገልግሎቱን እንዲያገኙ አድርጓል። ከእነዚህም መካከል በአነስተኛ ገቢ የሚተዳደሩ **76**ቱ የአካል ጉዳተኞች አገልግሎቱን በሚያገኙበት ወቅት የዓአቀመኮ የመጓጓዣና የምግብ ወጪያቸውን ሸፍኖላቸዋል።
- ለ**53** ታራሚዎች አጠቃላይ የአካላዊ መልሶ ማቋቋም ድጋፍ አድርጓል፤ ይህም የሰው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ እንዲሁም ክራንችና ዊልቼር መስጠትን ያካትታል።

## የሰብዓዊነት ህጉን ማስተዋወቅ/ኮሚኒኬሽን

እአአ ከጥር እስከ ሰኔ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ፤

- ከኦሮሚያ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ለተውጣጡ **35** የፖሊስ መኮንኖች በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት እና ሰብዓዊ መብት መስፈርቶች ላይ ያተኮረ (ከወንጀል ምርመራ ጋር በተገናኘ መልኩ) ስልጠና አዘጋጅቷል።
- ከአማራ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ለተውጣጡ ልዩ ፖሊስ ሀይል አዛገኖች በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግና ሰብዓዊ መብት መስፈርቶች ላይ ያተኮረ ስልጠና ሰጥቷል።
- ከኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ሀይል የደቡብ ክልል እዝ ለ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት እና ሰብዓዊ መብት መስፈርቶች ላይ ያተኮረ ስልጠና አዘጋጅቷል።
- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን የዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ ክሊኒክ ለማቋቋም የሚያስችል ድጋፍ አድርጓል።
- ከኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ጋር በኮቪድ-19 ወቅት ፖሊስ ሚናውን በአለም አቀፍና አገራዊ ህጎች መሠረት መወጣት እንዲችል እንዲሁም ማህበረሰቡ ስለበሽታው ያለውን ግንዛቤ ለማዳበር የሚረዱ መረጃዎችን የፖሊስ ሚዲያን በመጠቀም ለማሰራጨትና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ፈርሟል። በመግባቢያ ሰነዱ ስምምነት መሠረት **17,950** የእጅ ጓንቶች፣ **30448** ጭምብሎች፣ **600** ሊትር የእጅ ብክለት ማጽጃ ኬሚካልና **50** ድምጽ ማጉያዎች ለኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅና ኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽ ሰጥቷል።
- በማህበረሰብ ውስጥ ግንዛቤን ለማዳበር የሚረዱ መሰረታዊ መርሆዎችን፣ የዓቀመኮና የኢቀመማ ተግባራትን እንዲሁም ኮቪድ-19ን ለመከላከል የተወሰዱ እርምጃዎችን በሚመለከት ከ**100** በላይ መልዕክቶች በዓአቀመኮ ኢትዮጵያ ልዑክ የፌስቡክ ገፅ ላይ እንዲወጡ ተደርጓል።


## ከኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ጋር ያለው ትብብር

እአአ ከጥር እስከ ሰኔ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ፤

- የ**1,000** ተረጂ ሰዎች ፍላጎትን ሊሸፍን የሚችልና መሠረታዊ ቁሳቁስ የያዙ **1,000** ሳጥኖች (kits) ለኢቀመማ ሰጥቷል፡፡
- ኢቀመማ በመላ አገሪቱ ክልሎች የኮቭድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከል ለሚደርገው ጥረት/ትግል ምላሽ ለመስጠት እንዲችል ከ**2.7** ሚሊዮን ብር ለማህበሩ ለግሷል፡፡



በኦሮሚያ ክልል በባቢሌ ወረዳ በኤረር ኢባዳ ውስጥ በግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች የዘር እህል እርዳታ ሲቀበሉ (እአአ 2020 ዓ.ም)፡፡




ICRC


አድራሻ

Facebook.com/ICRC AFRICA
twitter.com/ICRC_Africa
Instagram.com /icrc.afrique

ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ
አዲስ አበባ ዋና መስሪያ ቤት
ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12/13
ፖ 5701
ስ 011647 8300
ፋ 011647 8301
ኢ-ሜይል: addis_abeba@icrc.org
Facebook.com/ICRCEthiopia
www.icrc.org

ነቀምት
ቀ 05, H.No. 290
ስ +251 576 606 655
ፋ +251 576 606 657

መቀሌ
ወ. ደቡብ, ቀበሌ 16
ስ +251 344 40 8353
ፋ +251 344 40 4540

ጅግጅጋ
ዞን 2 ቀ 10, ቤ.ቁ 0196
ስ +251 252 78 8149


የዓአቀመኮ በዓለም ዙሪያ በትጥቅ ግጭትና በሌሎች ብጥብጦች ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ስዎች ሰብዓዊ ክብራቸው እንዲጠበቅና የሚደርስባቸውን ስቃይ ለመቀነስ የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ ይህን የሚያደርገው በአብዛኛው ከቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ማህበራት ጋር በመተባበር ነው፡፡ እንዲሁም ድርጅቱ በግጭት ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን ተፅዕኖ/ስቃይ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግን በማራመድና በማጠናከር እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት መርሆዎችን በደንብ እንዲታወቁ ጥረት ያደርጋል፡፡